የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 49
ADDIS ABABA 15th July, 2013

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻/፪ሺ፭ ዓ.ም

በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..................ገጽ ፮ሺ፱፻፭

## CONTENTS

Proclamation No. 800/2013

African Development Fund Loan Agreement for Financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme in the Horn of Africa Ethiopia Project Ratification Proclamation ................................ Page 6905

## አዋጅ ቁጥር ፰፻/፪ሺ፭

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፴ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት (ሠላሳ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. በፌብሩዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

| | |
|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit Price | 2.30 |

## PROCLAMATION No. 800/2013

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 30,000,000 U.A (thirty million Units of Account) for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Program in the Horn of Africa: Ethiopia Project was signed in Addis Ababa on the 23rd day of February, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 25th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. በፌብሩዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150028344 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት (ሠላሳ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme in the Horn of Africa Ethiopia Project Ratification Proclamation No.800/2013".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number 2100150028344 signed in Addis Ababa on the 23rd day of February, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 30,000,000 U.A (thirty million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of July, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ